# የኢትዮጵያ ሕዝብ በጀግና መሪ እንጂ በድርጅት አምኖ አያውቅም!!

ይፍሩ ኃይሉ፣

እስከአሁን ስለኢትዮጵያ ታሪክ የተጻፉትን መጻጎፍትም ሁኑ የተልያዩ የጥናት ጽሑፎች  እንደ ተመልክትኩት፣ ሁሉም ባይሆኑ አብዛኞቹ "የኢትዮጵያ ታሪክ "ከአጼ …… ዘመነ መንግሥት እስከ አጼ ዘመነ መንግሥት ድረስ ብለው ሲጀምሩ እንጂ ከደርግ የደም ዘመንና የእልቂት ታሪክ እስከ ወያኔ (ሕወሐት) የዝርፊያና የመገነጣጠል፡የመግደልና የስደት፣ የሰቆቃ፣የአገር ማስግንጠል፣ የአገርናን ሃብት ለባዕዳን የመሸጥ ዘመን ተብሎ የተጻፈ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ያተኮረ አንድም ጽሁፍ እስከ አሁን ድረስ አላነበብኩም።

ምንም እንኳ የዘውድን ሥራት አናግቶ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ የመብቱ ባልቤት ለማድረግና አርሶ አደሩን □በሬ ለሚጭረው መሬት የባለቤትነት መብቱን እንዲከበር ባጭር ታጥቆ የታገለለት በተማሪው ንቅናቄ የተደፈው ኢሕፓ(የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ) ቢሆንም፣ እሱም የቀደደውን ፈር ተከትለው በኋላ እንደ አሸን የፈሉት የተለያዩ ድርጅቶች እንደነበሩ መካድ አይቻልም። ደርግም እራሱ እነዚህ ፓርቲዎች ከስር ከስራቸው እየተከታተለ እራሱንም ፣ ተከታዮቹንም በፓርቲ አዘጋጅቶ ነበር። በዚህም እርምጃው ነው ጥሩ "የከፋፍለህ ግዛ ዘዴው" ያስጉኛል ወይም ይቃወሙኛል ያላቸውን ሁሉ እርስ በራስቸው እንደዉሻ አናክሶ መሃል ከትማ ዉስጥ በመትረይስና በቺቺ እንዲታጣበሱና ዕዲተላለቁ ያደረገው።

የጽሑፌ መነሻውም ሆነ ዓላማው በፓርቲ ተደራጅቶ እዚህ ግባ የሚባል ለውጥ እስከአሁን ድረስ በአገራችን እዳልተመዘገበ ለማሳየት ስለሆነ በተቻለ መጠን ፋይዳቢስነቱን ለማሳየት እሞክራለሁ። ቀደም ብዬ እንደጠቀስክት ከተማሪው ንቅናቄ ወደ ፓርቲነት ወይም ድርጅት ከኢሕአፓ ወይም (E.P,R.P) የተለወጠው፣ ከዚያም እሱን ተከትለው የተፈለፈሉት ፓርቲዎችም □□ ደርግ በጉያው ያቀፋቸው ደጋፊዎቹ ተሰሚንትም ሆነ የተከታዮቻቸው ብዛት ከአዲአበባና ከአንዳንድ ከፍለ ሃገራት ዋና ዋና ከተማዎች ዉጭ ጨርሶ አልነበረም ማለት ይቻላል።

በነዚህም ከተሞች ዉስጥ አንግንተውት የነበረው ዝናና ተደማጭነት በጊዜው በነበሯቸው መሪዎቻቸው ፣ ተናግረው በሚያፈዙ፣ ጽፈው በሚያስረዱ፣ በወኔና በግርማ ሞገስ የታደሉ ፣ ቆራጥ መሪዎቻቸው እንደነበረ ማስረጃ የሚስፈገው፣ አይመስለኝም። እንደዋለልኝ መኮንን፣ እንደ ብርያነ መስቀል ረዳ፣ እንደ ኃይሌ ፊዳ ሌሎችም ፣ሌሎችም፣ በየተራ እየተምቱ እንደ ቅጠል ሲረግፉ፣ ድርጅታቸውና፣ የቆሙበት ዓላማ ቀስ በቀስ ብትትኑ እየወጣ፣ እንደጢስ በኖ ጠፋ። አውራው ሲሞት፣ ወይም ተመርሮ አገር ጥሎ ሲበር ቀፎው ባዶውን እንደሚቀር ሁሉ፣ እነዚያም ጊዜው የፈጠራቸው ድንቅ ምሑራንና ቆራጥ ጀግኖች ያለ ዕድሜያቸው ባጭር ሲቀጩ ድርጅታቸውም፣ ደጋፊዉቻቸውም አብረው ቀስ በቀስ አገር ጥለው ተስደዱ፣ በየአለበት ብትንትናቸው ወጣ። አንዳዶቹም እስከ መጨረቻው እነሱም እንደ መሪዎቻቸው እስከ ወዲያኛው ድረስ አንቀላፉ። ዕርግጥ ነው አሁንም የዚያ ትውልድ እርዝራዦች አልፎ አልፎ ድምጻቸው ይሰማል። ተመልሶ የማንሰራራትና ሊያመጡ የሚችሉት ለውጥ አለወይ ለሚለው ጥያቄ እንሱና ጊዜ ብቻ ናቸው የሚመልስት።

እንግዲህ "ከአጼ ኃይልስላሴ ዘመነ መንግሥት በፊት በፓርቲ የተዳራጀ ኃይል ወይም ቡድን ነብረ " የሚለኝ ካለ ለማዳመጥ ዝግጁ ነኝ። የማዳመጡም ሆነ ከሌሎች ተምሮ የመረዳት ችሎታ አለኝ። እንግዲህ አግዙኝ!!

እንግዲህ ፓርቲ ወይም ድርጅት ካልነበረ ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በምን ዓይነት ሥረዓት ሲተዳደር ቆይቶ ነው ይችን እጹብ ድንቅ የሆነች አገር፣ ዳር ድንበሯ ሳይደፈር፣ነጻነቷ ሳይገፈፍ፣ በዓለም ዙሪያ ተከብራና ተፈርታ እንድትኖር፣ ዛሬም ለኛ መኩሪያና መመኪያ ለመሆን የበቃችው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ብዙም መንዛዛትና መፈላሰፍ ሳያስፈልግ ፣ ሁለት ነገሮችን ማጤን ያሻል። አንደኛው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተ ክርስቲያን ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ሑለተኛውንና ዋና ትኩረት በምሰጥበት በኢትዮጵያ ቆራጥ ጀግኖች ልጆቿ ላይ ያጠነጠነ ይሆናል።

እኔ በሃይማኖት ውስጥ ገብቼ ለመዛጨትና የማንንም ሃይማኖት በሁለተኛ ደረጃ ለመመልከት አልቃጣም። ለዚህ ብቃቱም፣ መረጃውም የለኝም። በተለይም የስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ግሩም ድንቅ ኢትዮጵያውያን ውነንድሞችና እህቶቼን

ለማስቀየም ጨርሶ አልከጇለውም።ከሁሉም በላይ ይህ አቋሜ እንዲመዘገብልኝ እወዳለሁ።

በሥላጣኔው ደረጃ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ያበረከተችውን ዝርዝሩ ከመጫኛ የረዘመ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል።ምናልባትም ባለም የጥንት ሥልጣኔ ካስመዘገቡ ጥቂት አገሮች ብቸኛዋ ወይም የመጀመሪያዋ ባትሆንም እንኳ ከነሱ መካከል ( የግሪክና፤ የኪሜት ፤የዛሬይቷ ግብስጽ) መሃል መቆሟን ታሪክ ይመሰክርላታል። በራሳቸው ቋንቋ፤ በራሳቸው ፊድል፤የራሳቸው የቀን መቁጠርያና አሃዝ ወይም ቁጥር ካላቸው አገሮች፤አንዷ ኢትዮጵያ መሆኗ ሊዘነጋም አይገባም። ቀለም በጥብጠው፤ ከሸንበቆ በዕር አሹለው፤ ብራና ፍቀው ፤ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ መስፋፋት፤ መበልጸግና፤ የሚያስደንቀው የአገራችን ታሪክ በደንብ ተምዝግቦ ዛሬ ለኛ የደረሰው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ያላቋረጠ ጥረት ነው።

የቤተ ክህነቱ አወቃቀር እራሱ በአለቃና በምንዝር፤ በቀደም ተከተል የተዋቀረ በመሆኑ፤ከላይ ሊቀጳጳሱ በነበረው ሙሉ ሥልጣንና ተደማጭነት እንደ ነገሥታቱ ነጋሪት አስጎሽሞ፤ እምቢልታ አስነፍቶ ሳይሆን፤ አገሪቷ በችግር ላይ በወደቀች ጊዜ ፤ ቤተክህነትም የጓሮዋን ደወል አስደውላ፤ ከበሮዋን አስመትታ ፤ ካህናቱ ታቦት ተሸክሞ፤ወደ ጦር ግንባር እንዲጓዝ ታደርግ ነበር።ጳጳሱም ሆኑ ሊቀ ጳጳሱ በሕዝብ የነበራቸው ከበሬታና አድንቆት ከፍ ያለ ስለነበረ፤ትእዛዛቸውን “ ለምን?” ብሎ የሚጠይቅ አልነበረም። እንዲህ መሪዎችና የቤተ ክህነት አለቆች ከሕዝብ የነበራቸውን ተደማጭነትና የመሪነት ችሎታ ተቀብለው እነሱም የተጣለባቸውን ግዳጅ በትክክል ይወጡ ነበር።

ለኢትዮጵያ የሥላጣኔ ምንጭና መስረት ያለምንም ጥርጥር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለመሆኗየሚያከርክር ምክንያት ይቀርባል ብዬ አልጠብቅም። ካለም “ሸማ በየፈርጁ ይለበሳል”ነውና ሁሉንም እንዳመጣጡ ለማዳመጥ ዝግጁ ነኝ። የኢትዮጵያ ኦርትሆዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በዘመኑ በነበራት የሲሦ መንግሥት ድርሻ ፤በግንባር ቀደምትነት ስትወጣው የቆየቺው ግዳጇ ከቤተ ክህነት ኃላፊነቷም ባሻገር፤ እናት አገር ከውጪም ሆነ ከውስጥ ከሚነሱባት ጠላቶቿ ለመከላከል፤ ታቦት አሸክማ፤በቄስ ቀሳዉስቱና በዲያቆናት ካህናቱ ታጅባ፤ከጦር አዝማቾች ደጃዝማቾችና ፊታውራሪዎች እኩል በግንባር ቀደምትነት ትሰለፍ እንደነበረ የታሪክ መጽሐፍት ቁልጭ አድርገው ይመሰክራሉ።

ቤተክህነታችን የተራራቀን የምታቀራርብ፤የተጣላን የምታስታርቅ፤ቅዱስ ጋብቻን የምትባርክ፤የማያዛባ ሚዛን ያላት በመሀኗ፤ መሪውቿም በሕብረተሰቡ ላይ የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም።ዛሬም ለገጠማት ችግር “ማነው መሪው?”የሚለው ጥያቄ ነው እንጂ ቤተክህነት ምንድነች የሚለው አይደለም።የቤተ ክህነት መሪዎች በቃላቸው ብቻ የተመዘዘን ጎራዴ ወዳፎቱ የሚያስመልሱ፤ የተቃጣን ጦር፤የተደገነን ጠመንጃ የሚያቆሙ ፤ትዕዛዛቸው ወይም ግዝታቸው በሚመሩት ሕዝብ ላይ ያን ያህል ሥልጣን ያን ያህል ኃይል ነበረው።ስለዚህ በባሕላችን የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪውን እንጂ በሚወክለው ድርጅት ላይ ቁባ ቀዳዳ ኖሮት አያውቅም።

ቀደም በዬ ከላይ እንደ ገለጽኩት ፤በሁለተኛው ደረጃ ለማብራራት የምሞክረው ፤ የኢትዮጵያ የቀድሞ ነገሥታትም ሆኑ ጥሩ ስምና ዝና ትተው ያልፉ ጀግኖች ሎጆቿ ኢትዮጵያን አስቀድመው እንጂ ድርጅት ወክለው፤ሕዝብ የረመጣቸው፤አልነበሩም። በዘር ትውልድና በይገባኛል በዙፋን ላይ ተቀምጠው " አገር መራን፡ ሕዝብን አስተዳደርን" ይበሉ እንጂ ዕውነተኛው ሥራ ይቀላጠፍ የነበረው ከንጉሡ ነገሥቱ ወይም ከንግስቲቱ በታች የነበሩት መኳንንቶች ነበሩ።እነዚህ መኳንንቶችና ሹማምንቶች ከየመጡበት ቀዬ የሕዝብ አክብሮትና ተቀባይነት ስለነበራቸው፤ በዚያ ምንም የመገናኛ መዋቅር ባልነበረበት ዘመን በስማ በለው ብቻ ሥራቸውንና ግዳጃቸውን በቅልጥፍና ይወጡት ነበር። ምን ጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚያምንበትና ለሚያከብረው መሪ ሙሉ ትብብሩን ከመለገስ ተቆጥቦ አያውቅም።

አንዳንዱም እናቱ የወለደቺው ቀልጣፋ ወንድ " ጀግናን ጀግና አይገዛውም" ይልና ገብቶበት ከነበረው ቀለበት ዉስጥ አፈንግጦ ይወጣል።

**"ጀግናው ለጀግና አድሮ ሳያውቀው ብልሃቱን፤**

**“ሲለምን ያመሻል እንደ ዉሻ እራቱን" የሚለው ትዝ ሲለው ፡አሻፈረኝ!!”** ይልና መሳሪያ አንግቶ፤ የአለቃውን ሥልጣን ተቀናቃኝነቱን በይፋ ያውጃል። እዚህ ላይ መይሳው ካሳ ትዝ ሊለን ይገባል። መይሳው ሲሸፍት ስንቱ ቆራጥ ጀግና እንደተከተለው የምንዘነጋ አይመስለኝም። እነ ፊታውራሪ ገብርዬ የምሳሰሉ እራሳቸውን የቻሉ ቆራጦች ለምን መይሳውን ለመከተል መረጡ? ለምን ለመይሳው" እኔ ያንተ አሽከር እያሉ መፎከርን ወደዱ? መልሱ አንድና አንድ ብቻ ነው፤ በመይሳው ይተማመኑ፤ ከሱ ጋር መጓዙ ከዳር እንድሚያደርሳቸው ያውቁ ስለነበረ ነው። ጀግና ሁልጊዜም ይወደዳል፤

ስሙ ከማር ከወተት ይጣፍጣል።

የከጀመርን አይቀር እስኪ ወደ ትግራይ ተጉዘን አጼ ዮሐንስን እንጎብኛቸው። ከአጼ ቴዎድሮስ ዕረፍት በኋላ በትረ መንግሥቱን የተቀበሉት አጼ ዮሐንስ ገጥሟቸው ከነበረው አሳሳቢ ችግሮች መሃል አንዱ የድሩቡሾች በኢትዮጵያ ላይ እይናቸውን በመጣላቸው ያንን አሳሳቢ ችግር ፊት ለፊት ትጋፍጠው ከአገራቸው ጠላት ጋራ ተፋልመው፤ አይቀጡ ቅጣት ቀጥተው፤ የናት አገራቸውን ዳርድንበር ሊያስገብሩ፤ሠራዊታቸውን ክተት ብለው ወደመተማ ተጓዙ። ጀግናው ዮሐንስ በድንኳን ውስጥ ተቀምጠው አልነበረም ጦርነቱን የሚመሩት። እሳቸው፤ እራሳቸው ግንባር ቀድመው፤ በያዙት የእንግሊዝ ዲሞትፈር እያርበደብዱት፤ ወታደራቸውን "ግፋበለው" እያሉ ሲዋጉ ክፉኛ በጠላት ጥይት ተመተው ወደቁ፤ ሰራዊቱ ተረባርቦ ቁስለኛውን ጀግና ከድንኳን ዉስጥ አስግብተው ማስታመም ተጀመረ። ለሠራዊቱ ጃንሆይ ቆስለዋል፤ አሁን ይመላሳሉና ወደፊት ግፋ ተባለ። ግን ምን ያደርጋል የዮሐንስ ቁስል ቀላል አልነበረም። ካህናቱና የንጉሱ ባለሟሎች ንጉሡ እንደማይተርፉ ስለአወቁ ሁኔታውን በጠበቀ ሚስጢር እንዲያዝ አደረጉ። ሌሊቱ ላይ ጀግናው ዮሃንስ እስከ መጨረሻው አንቀላፉ። ካህናቱ አስከሬኑን ከቦ እጣኑን እያጨሰ ሲያዜምና ሲዝምር አደረ። አሁንም የጉሡ መሞት ለሠራዊቱ አልተነገረውም ነበር።ጠላትም መቁሰላቸውን እንጂ እረፍታቸውን ገና አላወቀም ነበር። ለምን ይሁሉ ጥንቃቄ አስፈለገ። የንጉሡ መሞት ከጠላት ጆሮ ቢደርስ የላሸቀው ሞራሉ ተንሰራርቶ ከመከላከል ወደ ማጥቃት ይሸጋገራል። በዚሁ መጠን ደግም የዮሐንስ ሠራዊት ውኔው ይሰበራል፤ መደናግጥና መርበትበት ሥፍራ ያገኛሉ። ልክ እንድተፈራውም የንጉሱን መሞት ጠላት ሲሰማ ኃይሉን አጥናክሮ የዮሐንስን ምሽግ ሰብሮ ገባ፤ አስከሬኑን ማረከ። በአረመኔው እጁ የንጉሱን አንገት ቆርጦ ለሠራውቱ አሳየ። መተማ ላይ ዮሓንስ አንገቱን ለካራ ገብሮ የኢትዮጵያ ሠራዊት ድል ተመታ።አውራው ዮሐንስ፤ መሪው ዮሐንስ፤ አዝማቹ ዮሐንስ ሲወድቅ ሠራዊቱም የመዋጋት ኃይሉንም ፍላጎቱምን አጣው። አሞቱ ፈሰሰ።

መቼም ኢትዮጵያ ከውጪ ወራሪ ጠላት ጋራ ባደረግቺው ተጋድሎ የማያኮራ ውጤት ያስመዘገበቺው በማይጮው ጣርነት ላይ ነው። የፋሽስት ጦር "የኢትዮጵያን ሠራዊት ደምስሼ አዲስ አበባን ለማያዝ ከስድስት ወር እስከ አንድ ዕመት ይወስዳል" ያለውን፤ የማይጮውን ጦርነትለማሸነፍ የወስደበት ጊዜ አራት ቀን ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ ለጣሊያን መንገዱ አልጋ በአልጋ ነበር"።

አጼ ኃይለ ሥላሴ በስንት ጣርና መከራ ነፍሳቸው አዲስ አበባ ደርሳ፤ ብዙም ሳይቆዩ በጂቡቲ በኩል ወደ እንግሊዝ አገር ሲሰደዱ፤ ሕዝባቸውንና አገራቸውን ለማን አደራ ብለው እንደሄዱ እስከ ዛሬ ድረስ አጥጋቢ መልስ አላገኘሁም፤ንጉሡ ነገስቱ እንግሊዝ አገር ከደረሱ በኋላ፤ በእንግሊዝ መንግሥት መከላከያ ጥላስር ተቀምጠው፤በተረጋጋ መንፈስ ላገራቸው ያደረጉት ትግል እንዳለ ሆኖ፤አገርቤት በትነዋቸው የመጡትን አርበኞች እጣ ፋንታ መመርመር ይኖርብናል። የሚገርመው ጃንሆይን ጂቡቲ ድረስ የሸኟቸውን አርበኞች ተከትላቺሁኝ ሂዱ ብለው  የጠየቋቸው አርበኞች ነበሩ። ከነዚህ አርበኞች መሃል አንዱ ደጃዝማች ተሰማ እርገጤ ነበሩ። " ጃንሆይ የጠላትን ኃይል አይተውታል! እርስዎ ይሂዱ እኔ አገሬ ተመልሼ ዉጊያውን እቀጥላለሁ ብለው እንደቀሩ ደጃዝማች ነግረውኛል።እንግዲህ እንደ ደጃዝማች ተሰማ እርገጤ ያሉ ጀግኖች ናቸው ወደ ትውልድ አገራቸው እየገቡ ገበሬና ጎልማሳውን አስተባበረው ጠላትን አምስት ዓመት ሙሉ በዱር በገደሉ እያራወጡ፤ ጠላት እፎይ ብሎ እንዳይተኛ እንቅልፍ እየነሱ፤ በመጨረሻም የጣልያንን ጦር ድባቅ መተው ለድል ያበቁን። መቼም ስለአርበኞች ሲነሳ እራስ አበበ አረጋይ ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው የጦር መሪ ሆነው እናገኛቸዋለን። ጠላት አዲስ አበባን ሲቆጣጠር፤ እራስ አበበ የአዲስ አበባ ከቲባ ነበሩ። እንደ አገራችን ልማድና ባሕል ወንድ ልጅ ካባቱ ፈርስ መጋለብን፤አነጣጥሮ መተኮስን፤ ጊጤና ጉግስ ጨዋታን ያውቁ ነብር እንጂ ሌላ ምንም የጦር ስልት አያውቁም ነበር። ስመጥሩው ጀግና በላይ አባኮስትርና፤ እራሳቸው ተሰማ እርገጤም፤ አብዛኞቹ ነፍጥ አንስተው "ጎራው ቤቴ" ያሉት ተራ ገበሬዎች ነበሩ። ግን ሕዝብን የማስተባበርና የሕዝብን ስሜት የመቀስቀስ ችሎታ ስለነበራቸው ሕዝቡም "የገሌን ጦር እቀላቀላለሁ" እያለ ተከተላቸው እንጂ የማን ድርጅት ነው? ብሎ አልጠየቀም።

**“ተመልከት ዓላማህን"**

**“ ተከተል አለቃህን"** ነውና ዓላማቸው ንጻነትን መጎናጸፍን ብቻ ስለነበረ፤ "ወደ ነጻነት እመራችኋለሁ ያለውን መሪ ያምኑታል፤ ያከብሩታል፤ጀግንነቱን ካስመሰከረ ፤ "ተከተል አለቃህን "የሚለውን ተመክሮ አጥብቀው ያምኑበት ነበር።

አሁንስ በቅርቡ የኢትዮጵያ ሠራዊት እንክትክት ብሎ የወደቀውና ብትንትኑ ሊወጣ የቻለው በምን ምክንያት ንው? የመንግሥቱ ኃይለማርያም አገር ጥሎ መፈርጠጥ ባይሰማ ኖሮ ሌላው ቢቀር አዲስ አበባ እየተከላከለ፤ በር ዘግቶ ቢሆን ኖሮ

አንደኛ ወያኔን ሳይወድ በግድ ወደ ሰላም ውይይት እንዲመጣ ያስገድደው ነበር፤ ሑለተኛ ሕዝብ አብሮት ተሰልፎ ድጋፉን ይሰጠው ነበር እንጂ በምንም ዕይነት ተአምር፤ወያኔን ሆ! ብሎ ሕዝብ ይቀበለው ነብር ብሎ የሚያን፤ያለ አይመስለኝም ፤ ቢኖሩም ያው የወያኔ ዘር ምዛሮችና ኤርትራውያን ይሆናሉ። ከዚያ ውጪ ምን መትረየስ ቢደገንበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን አይቀበልም። ነገሩ የተበላሸው፤ ከፋም ለማም መንግሥቱ ኃይለማርያም የአገሪቱ መሪ ስለነበረ፤ሌላው ቢቀር የሠራዊቱን ልብ ስርጾ የገባ ስለነበረ፤ እሱ ጥሏቸው ሲፈረጥጥ የሠራዊቱም ሞራል ተንከታክቶ ወደቀ፤ብዙም ሳይቅይ መዳሊያውን እያነጠፈ ልመናውን ተያያዘው። ይገርማል፡ክላሽኒኮፍ አንግቶ ወንድ ልጅ ሲለምን ይገርማል !ይደንቃል። የኔ የባላገር ዘመዶቼ እንኳ ባለቻቸው አቅምና ወኔ የሚያንጎራጉሯት ወኔን ትቀሰቅሳለች፤ የሞተን ታስነሳለች።

"እምቢ አፋፎረኝ አልወድም ፈሪ"

"ምንሽር ይዞ ድንጋይ ወርዋሪ"

"እንደ አዲስ ምድር እህል ደፋሪ" ይሉ ነበር። የኔ ወገኖች የሚጠሉትና የማይወዱት ነገር ቢኖር፤ጥቃትን፤ፈሪና ሁዳምን ነው። ዛሬ እነዚያ ጀግኖች በሕይወት የሉም፤ ጥሩ ስማቸውንና የማልረሳውን ፍቅራቸውን ብቻ ተተውልኝ አልፈዋል።

ደርግ ተንከታክቶ ከመውድደቁ በፊት በዚህ በሰሜን አሜሪካ፤ ዓይኑን ፍጥጥ አድርጎ ኢትዮጵያን የሚጠብቃትን አስፈሪ የመከራ ዘመን ቀደም ብለው የተረዱ ድንቅ ኢትዮጵያውያን በዋሽንግተን ዲሲ መሰባሰብና መወያየት ሲጀመር ፤በርካታ ስመ ጥሩ ኢትዮጵያውያን ነበሩበት። ከነዚህ መሃል አንዱ ኮሎኔል ጎሹ ወልዴ ነበሩ። ኮሎኔሉ ይዘውት ክመጡት ወደር የሌለው የሥራልምዳቸው፤ በወታደራዊ የጦር ስልትና፤ ከሚያስደንቀው የትምህርት ክንውናቸውጋራ ተደማምሮ እሳቸው ጎልተውና ደምቀው እንዲታዩ አድርጓቸው ነበር። ከሁሉም ይበልጥ ግን የኮሎኔሉ የዘር ግንድ የበቀለው ከሰፊው የኦሮሞ ማሕጸን ስለነበረ፤"፡ትክክለኛው ሰው፤ በአስፈላጊው ሰአት፤ለሚያስፈልገው ሥራ ተገኘ" ብለን ሁላችንም እልልልብለን ተቀበልናቸው። የኮሎኔል ጎሹ ወደ ትግሉ በሙሉ ልብ መምጣት አሜሪካን ተሻግሮ በዓለም ዙሪያ ተሰራጨ። ከአውሮፓ፤ እስከ ኒውዚላንድ ፤አውስትራልያ፤ ክደቡብ አፍሪካ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ ተሰራጨ። በኮሎኔል ጎሹ መሪነት፤ በተከተላቸው ሕዝብ ቆራጥነት ዓይን ስንገመግመው "አዲዮስ ወያኔ ከንግዲህ እድሜህን በቀን ቁጠር፤ የመጣህባቸውን አህዮች ሰብስብና ጉዞህን ጠቅልለህ፤ ስንቅህን ጭነህ ወደ ደደቢት ተመለስ" እያልን ፈነደቅን። ግን ምን ያደርጋል! ደስታችን ዘላቂ ሆነ ለፍሬ ሳንበቃ ቀረን። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ነበሩ።

አንደኛ/ ኮሎኔሉ እራሱን የቻለ፤የሰው ልጅ ሊሸከመው የምይችል፤ የግል ፈተና ገጥሟቸው ነበር።(ዝርዝሩን ከመስጠት በግድ እቆጠባለሁ)

ሑለተኛ፤ በመድኅን ዉስጥ ሰርገው የገቡ፤የወያኔ ሰላይ ግለሰቦች፤ባለ መታከትና ባለማቋረጥ በኮሎኔሉ ላይ የጎን ውጋት ሆኑ፤ በጭራሽ መፈናፈኛ አስጥተው፤ ትግሉ ወደፊት እንዳይራመድ፤ ባለበት እንዲቆም፤ ብሎም ጨርሶ እንዲጠፋ አደረጉ። መድኅን ለሁለት ተከፈለ፤ እየተዳከመም ሄደ በመጨረሻም ኮሎኔሉ "ፖሊቲካ በቃኝ" ብለው

እራሳቸውን አገለሉ። እኛም ልጆቿ ጥሩ መሪ አጣን። አገራችን ኢትዮጵያም ለመጀመሪያ ጊዜ በዋለበት ጎራ፤ በቆመበት አደባባይ በኩራትና በመተማመን ሊያገለግላት የሚችለውን ልጇን ተስፋ እንዲቅርጥ አደረግን።

የሰሞኑ መወያያ ልበለው መነታረኪያ የሆነው የዶክተር ብርሃኑ ነጋ የአርበኞችግንቦት7ን ሠራዊት ለመቀላቀል ወደ ኤርትራ መግባታቸው ነው። ለተቃውሞው ወይም ለንትርኩ ምክንያት የሆነው ለምን በኤርትራ? ከኤርትራ ምን በጎ ነገር ይጠበቃል? የመሳሰሉት ናቸው። እኔ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ጽፌአለሁ፤ከብዙዎች ጋራ ዱላ ቀረሽ ተከራክሪያለሁ።። "ብዞዎች ግንቦት 7 ከመኖሩ በፊት ጳጉሜ 7 ይኖረናል" ብለው የነገሩኝ ሞልተዋል። " ብርሃኑ ነጋ ሲያወራ አነጋ መሆኑን አታውቅም ወይ? እንዲያውም ግንቦት 7 የተፈጠረው ወይም፤ የተቋቋመው ዲያስፖራውን ለማወንበድና አቅጣጭውን ለማሳት፤ ወያኔ እራሱ የፈጠረው ድርጅት ነው" ብለውም የነገሩኝ ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም። ከሁልም ይበልጥግን የዶክተር ብርሃኑን ዕውነተኛ ሞቲቭ ለአማራው ሕዝብ ያላቸውን ስር የሰደደ ጥላቻ የሚያንጸባርቅ ሠዕል ሥለው ሊያስረዱኝ የሞከሩም ሞልተዋል። በመጨረሻም የዶክተር ብርሃኑን ወኔብስንት በማስረጃ እየደገፉ ሊያሳዩኝ የጣሩም አሉ። ሁሉንም አምዛዝኜ እኔ እራሴ የኢትዮጵያንና የኤርትራውን ጋብቻ አውግዤ የሚያስከትለውንም መዘዝ ዘርዝሬ ጽፌያለሁ።እኔ ወያኔንና ኤርትራን በጭራሽ ለይቼ አላያችውም። ለኔ ሁለቱም እኩል የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ናቸው። አሁንም ያቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ተልእኮ "፡ኢትዮጵያዊ ነኝ" ይሚለውን ሁሉ ባንድ ላይ ሰብስቦ፤ በአንድ ካምፕ ዉስጥ አጉሮ በመትረየስ ለመጨፍጨፍ ያቀደው የተንኮል ንድፍ እንጂ በውነትስ ለኢሳያስ አፈውርቂ የኢትዮጵያ ጭንቅና መከራ ይገደዋል ብዬ ለናኖ ሰኮንድ እንኳ

አልታለልም። ግንቦት 7 ምን ያህል ቢጨነቅና ቢቸገር ነው ኢሳያስን አስጠጋኝ ብሎ ሙጥኝ ያለው? ይህን ሳስብ ታዲያ የአቶ ከበደ ሚካኤል አንዲት ግጥም ትዝ አለቺኝ፡

*" በቸገረው ጊዜ የሚያዋየው ያጣ"*

***"ያካፍላል አሉ ጭንቁን ለባላንጣ"*** የምትለዋ፡(ከዕውቀትብልጭታመጽሐፋቸው **የተወሰደች**) **እይ!** ግንቦትሰባቶች ምን ያህል ጭንቅ ቢበዛባችሁ ነው ዘላችሁ ከጅብ ጎሬ ዉስጥ ልትገቡ የቃጣችሁ! ብዬ ተናግሬአለሁ። አድማጭ ቢጠፋ፡ መቼም የኔ ብጤ ጉጉ ነውና ምናልባት ለኔ የተሰወረ፤ ለነሱ ግልጽ የሆነ ምስጢር ይኖር ይሆን? ብዬ አሁንም እየተጠራጠርኩ ጓጓሁ። የኔ አቋም በዚህ እንዳለ አቶ ኤሊያስ ክፍሌ በድሕረ ገሱ ላይ በግንቦት7 ላይ ያለውን አቋም፤" መረጃ አለኝ" ብሎ ግንቦት 7 የቀን ቅዠት እንጂ በጭራሽ የሌለ ድርጅት ነው፤ ብሎ ምስቅልቅሉን አወጣው። ለዚህ የተሰጠው መልስና የወረደበት ዉርጂብኝ ሳነብ፤ አቶ ኤሊያስ ክፍሌ ስለግንቦት 7 የጻፈው ትክክል ካልሆነ ለምንድነው ግንቦት ሰባቶች ቡራ ከረዩ የሚሉት? አቶ ኤሊያስ ክፍሌን " አትተንፍስ፤ ያልንህን ሰምተህ ተቀብል" ለማለትስ ምን መብት አላቸው? ብዬ የተሰማኝን ቅሬታ "የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው" በሚል አረእስት ጽፌ፤ በውን ግንቦት 7 መሣሪያ አንስቶ የሚንቀሳቀስ ለመሆኑ እስኪ በሥራ አሳዩን፤ አልኩ። እናንተ አንዲት ጥይት አጩሃችሁ አንድ ወያኔ ስትገድሉ እኔ ያለኝን ድጋፍ በአደባባይ ለመግልጽና ባለኝ አቅም ሁሉ ከጎናችሁ ለመሰልፍ ዝግጁ ነኝ፤ ብዬ የኔንም አቋም እንደገና አብራርቼ ገለጽኩ።

ብዙም አልቆየንም " ፊሽካው ተነፋ፤ አርበኞች ግንቦት ሰባት ወያኔን ገጥሞ ድል በድል እየተቀዳጀ ነው" የሚል ዜና በኢሳት በኩል ታወጀልን። ማመን እያቃተኝ በድስታ ፈነድቅሁ፤የግንቦት ሰባት አባላት ወዳጆቼ " ነግረንህ ነበር አሁን አየሁ አይደል?" እያሉ በኤርትራ ላይ ያለኝን አቋምና ስለግንቦትሰባትም የነበረኝ ቅሬታ ትክክል

እናዳልሆነ ተነገረኝ። እንግዲህ አንድ ጊዜ ወንድሜ እሳቱ ዉስጥ ዘሎ ከግባ በኋላ ለምን ከሳት ገባህ? የሚለው ቁጣና ንዴት የተሞላበት ጩኸት ከማሰማት ይልቅ " ወንድሜን ከዚህ እሳት ዉስጥ እንዴት ላወጣው እችላለሁ?የሚለው ጥያቄ ቀደመብኝ። በምሳሌ ለማስረዳት የናቴን ልጅ ወንድሜን አቀረብኩ።

***"ወንድሜ ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት፤ ከጥሩ አካባቢ ቤት ገዝቶ፤ ሕግ አክሮ፤ እግዚአብሔርን ፈርቶ፤መካከለኛ ኑሮ የሚኖር ጥሩ ዜጋ ነው። ግን አንድ ችግር አለው፡ይኸውም ክርጎረቤቱ ጋር ተስማምቶ ሊኖር አልቻለም። አንድ ቀን ከቤቱ ይመጣና የገጥገመውን ችግር ግልጾ ይነግረኛል። እኔም እስኪ እንደሱ አስተሳሰብ ሳይሆን አንተ በፍቅርና በደግነት ቅሬታህን ንገረውና በሰላም ጨርሰው ብዬ አስናብተዋለሁ።ብዙም ሳይቆይ እንደገና ይመሰስና ያ የገጠው ችግር እየተባባሰ መሄዱን አብራርቶ ይነግረኛል። ያልተነካ ግልግል ያውቃል ነውና አሁንም ይህ ችግር በሰላም ሊፈታ እንድሚቻል ስነግረው በጣም ይቆጣና " ይህን ባለጌ አጨሰዋለሁ እንጂ እሱ ሰላም ምን እንደሆነ አያውቅም" ይለኛል። እኔም መልሼ እስኪ እረጋ በል፤ እሱም አይጨስም! አንተም አታጨስም! የሚያስከትለውን መዘዝ መግንዘብ ይኖርብሃል። ሁለተኛ ይህን ሃሳብ ይዘህ አጠገቤ እንዳትደርስ ብዬ ተቆጥቼ እመልሰዋለሁ።***

***የፈሩት ይደርሳል ይባላልና አንድ ቀን ወንድሜ ቁና ቁና እየተነፈሰ ከቤቴ ይመጣና " ያንን ባለጌ ገላገልኩት፤ እኔም ተገላገንኩ" ይለኛል። ምን ማለትህ ነው? ብዬ ስጠይቅ " በንባሩ አስገባሁበት!" ይለኛል። እጤ ዱብ ይላል፡ የናቴ ልጅ ወንድሜ ሚስትና ልጆቹን በትኖ ከሳት ውስጥ ገብቷል።እንደ ወንድም ምንድን ነው ማድረግ የምችለው? አሁን ለቁጣና ለንዴት ጊዜው አይደለም። ወንድሜ ከገባበት መዘዝ ለማውጣት ዘዴና ብልሃቱን መፈለግና በዚህ የጭንቁ ሰዓት ከጎኑ ቆሜ " አይዞህ አለሁልህ ከማለት በስተቀር " ምነው ተው አይሆንም ብዬ ነግሬህ!" እያልኩ መጨቅጨቅ ይገባኛል***?

ዶክተር ብርሃኑ ነጋም የወሰደው እርምጃ ሲስብከውና ሲያውጀው የነበረውን የትጥቅ ትግል ነው በሥራ ላይ እያዋለ ያለው። ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ከሱ ጋራ አብረው ተጋፍጠዋል። ዛሬ "ግጠህ ተወጣው" ለማለት የሕሊና ብቃት አለን? " እዚህ ቁጭ ብሎ፤ ቢራውን እየጠጣ፤ ሃምበርገሩን የገመጠ፤ ስለ ትጥቅ ትግል ያወራል። ወንድ ከሆነ እሱ አይሄድም? እያልን ትላንት የምናብጠለጥለው ብርሃኑ ነጋ ዛሬ ዘሎ ከሳት ዉስጥ ገብቷል። ትላንት የሱን ወኔ ቢስነት አጉልተን እያብራራን ቁም ስቅሉን የምናሳጣው ብርሃኑ ነጋ ነው ወኔውንና ቆራጥነቱን አግኝቶት፤ሚስትና ልጆቹን በትኖ፤ የተደላደለ ኑሮውን አሽቀንጥሮ ጥሎ፤ ዛሬ ዱሩ ቤቴ ያለው። የማይካደው ያቅ ግን እኔም እናትም ዛሬም እዚሁ አሜሪካ ተቀምጠን ጸጉር ስንጠቃውን እየተራቀቅንበት ያለነው።እንደ ልማዳችን ለኛ ዛሬም ሰማይ ቅርብ ነች ። ምነው ጃል መጃጃሉን ትተን ወገባችንን ጠበቅ አድረገን ታጥቀን ሌላው ቢቀር አንኳ ስንቁን ባገልግል እያቀብልን፤"አይዟችሁ በርቱ! በዲፕሎማሲውና በፖሊቲካው መስክ

እኛ ከዚህ አለን ። እናንተ ከዚያ በርቱ" ማለት እንዴት ያቅተናል።

ሰማይ ቅርቦችና ጸጉር ሰንጣቂዎች፤ ወደዳችሁም ጠላችሁም፤ ብርሃኑ ነጋ ታሪክ እየሠራ ነው። ባያርስ እያጣመደ ነው። የሱ የትጥቅ ትግሉን መቀልቀል ዜና ሲሰማ በውጣቱ ትውልድና በአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ያመጣውን ደስታ ጆሯችሁን ከፍታችሁ አድምጡ። ሑልጊዜ "እኛ ብቻ እናውቃለን" እያሉ የባጥ የቋጡን ከመቀባጠር አንዳንድ ጊዜ መዳመጡ ማለፊያ ነዋና እስኪ ጆሯችሁን ጣል ከማድረግ አትቆጠቡ። የብርሃኑ ነጋ ከሠራዊቱ በመሃል መገኘት በተዋጊው ሠራዊትና፤ የወያኔ ግፍና በደል ላንገበገበው ወጣት ምን ያህል ለውጥ እንደሚያመጣ መገመት እንዴት ያቅታል?፡ከጽሁፌ መነሻ ጀምሬ እንደ ገለጽኩት እኛ ኢትዮጵያውያን በጀግና መሪ እናምናለን። ጀግናን የመከተል፤ጀግናን የማድነቅ ልማድ አለን።እስኪ ትንሽ ቆጠብ ብለን የሚያመጣውን ለውጥ እንመልከት። ሌላው ቢቀር ወያኔን በየአቅጣጫው ተወጥሮ የጥይት ማዕበል ሲወርድበት፤ " ምነው ጎበዝ! እንዴት እንተላለቅ! ይህን ጉዳይ በሰላም ተወያይተን እንጨርሰው።" ብሎ ወያኔ ወደ እርቁ ጠረጴንዛ ቢመጣ ድሉ የማነው ትላላችሁ?የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያስረዱት "ወያኔ አለኝ የሚለው ሠራዊት ምንኛ ሞራሉ የላሸቀና፤ በዘር፤ በአድለዎና በሙስና የተዘፈቀና የተጨማለቀ መሆኑን የሚያስረዱ ብዙ ባለ ሙያዎች ተንትነውታል። ወያኔን የቆመባት መሬት እየከዳችው ነው። ይልቁንስ ከወያኔ ተንከታክቶ መውደቅ በኋላ የአገሪቱን ዕጣ ፋንታምን ይሆናል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሞክሩ።

እኔ ብርሃኑ ነጋን ለመጀመርያ ጊዜ የተዋወቅሁት ከውያኔ መግባት በፊት፤ በግንቦት ወር መጨረሻ ላይ (መሞሪያል ዊከኤንድ በኒው ስኩል ይደረግ በነበረው የአፍሪካ ቀንድ ስብሰባ ላይ ሊቀመበር ሆኖ ሽር ጉድ ሲል ነው። በዚያም ስብሰባ ላይ ለምን ለኤርትራይኖች ጥያቄ የመጠየቅና ሃሳባቸውን እንዲያብራሩ መድረክ እየሰጠህ እንዴት ታስደበናለህ? ብዬ በቅሬታ መለያይታችንን አስታውሳለሁ። ከዚያ በኋላ ወያኔ አዲስ አበባን ተቆጣጥሮ ሲገባ፤ ዶክተር ብርሃኑም ወደ አገሩ መግባቱን ሰማሁ። ከዚያም ቀጥሎ በ2005 (1997) ጠቅላላ ምርጫ ላይ ተቀዋሚ ኃይሎችን ተቀላቅሎ ወያኔን በየውይይቱ መድረክ ላይ እራቁቱን ሲያስቀረው በቴሌቪዥን  መስኮት ስመለከት፤ ለዶክተር ብርሃኑ የነበረኝ አስተያየት ተለወጠ። ከዚያ በኋላ የተፈጠረውን መዘርዘር መንዛዛት ስለሚሆን፤ ልለፈውና እንደገና አሜሪካ ተገናኘን። ግንቦት ሰባት ተመሰረተ፤ ሑለገብ የትጥቅ ትግል  በዶክተሩ እየተመራ ሰሜን አሜሪካ መቋቋሙ ታወጀ። ድንቄም የትጥቅ ትግልቅ ትግል! አልኩ። በተለይም የግንቦት ሰባት የሚሰለጥነውና ወታደራዊና የቆሳቁስ ድጋፍ ምንጩ ኤርትራ ነው ሲባል፤ ቀልድ ይቁም አልኩ። አህያን ጅብ ቢያባርራት አንበሳን እባክህ አድነኝ ብላ አትማጸንም አልኩ። በዚህ እንደከፋኝና እንደ አኮረፍኩ ይባስ ብለው ዶክተር ብርሃኑ የተስፋዬ ገብረ አብን መጽሐፍ ገምገመው፤ጸሐፊውን አድንቀው መጽሐፉን ማንበብ እንደሚገባን አሳሳቡን። ዶክተር ብርሃኑ ይህን መጽሃፍ የሚደግፉት ከሆነ፤በተስፋዬ ገብረአብ ላይ የነበረኝን ስር የሰደደ ቂም ወድጎን አድርጌ የታባለውን ዝባዝንኬ አነበብኩ።እነደተለመደው በመርዘኛ በእሩ " የኦሮሞ ሕዝብ ተስተህ አማራውን ጨፍችፈው" ነው። እኔም ሳልውል ሳላድር የተስፋዬን ባንዳነትና ለኤርትራ የቆመ ሰላይነቱን ቁልጭ አድርጌ፤የኢትዮፕያ ጉዳይ እሱን እንደማይመለከተውና ከእንግዲህ ጣልቃ ገብቶ እንዳዳክር አስጠንቅቄ ግልጽ ደብዳቤ ጻፍኩለት። መልስ የመጣልኝ ከተስፋዬ ገብረአብ ሳይሆን በቀጥታ ከግንቦት ሰባት ደጋፊዎች ነበር። በኔ ላይ ያወረዱት የስድብ ውርጅብኝ አንሶ፤ኢትዮመዲያንም "ለምን አተማችሁ!”ተብለው ብዙ ተወቀሱ።በነገራችን ላይ የተስፋዬ ሰላይነት በማስረጃ ተደግፎ ይፋ ሆኖ ከመውጣቱ በፊት ማንነቱን ቁልጭ አድርጌ የነገርኩት እኔ ነኝ።

አሁን "ለምን ዶከትር ብርሃኑ ነጋን ደገፍህ" ተብዬ ለሚወነጨፍብኝ ዘለፋ ለያንዳዱ መልስ ለመስጠት እቸገራለሁ።እኔ ለንባብ በማቀርባቸው ጽሑፎቼ ላይ ከሕዝብ በማገኘው ምስጋና ወይም ወቀሳ ብዙም ቦታ አልሰጠውም።"በርታ ቀጥልበት" የምለው ደስ አሰኝቶኝ አልፈነድቅም፤በዚሁም ልክ በሚደርስብኝ ወቀሳና ለቀፋም አልበሳጭም፤ ተስፋም አልቆርጥም። ግን ለዛሬው ባጭሩ የማምንበትን ዋና ምክንያት አጠር ባለች ዕውነተኛ ታርክ እጅምርና ጽሑፌን  እቋጫለሁ።

*የታሪኬ መነሻ  ይፋት፤ቀወት ልዩ ስሙ ጠጠርአምባ ይጀምራል።በዚች መንደር ውስጥ አቶ ውልደየስ የሚባል የሶስት ወንዶች ልጆችአባት፤አርሶ አደር ገበሬ ነበረ። ይህ ሰው በአራሽ ገበሬነቱ፤ የጤፉ ክምር ከሩቅ የሚታይ፤ ጥገት ላም ጊደሩ፤ ሰንጋና መሲናው በረቱን የሞላው ቀጭን ጌታ ከመህኑም ይልቅ ይበልጥ የሚታወቀው በጀግንነቱና  በሚጭናት ሰጋር በቅሎ፤ በሚጋልበው ሰንጋ ፈርስ፤ በሚይዘው ምርጥ መሳርያ፤ነበር። የሚገርመው ሁለቱ ልጆቹ እናዳባታቸው ባለዝና ጅግኖች ናቸው እየትባለ ድፍን ቀወት ያደንቃቸዋል። ባለመታደል የመጨረሻው ልጃቸው“ፈሪ ነው፣ ጨርሶ ያባቱ ወኔ በሱ ውስጥ የለም" እየተባለ ይወራበታል። እሱም  "አይ ያለመታደሌ እንዲያው ምን ብሠራ ነው የሕዝብን አክብሮትና ተቀባይነት የማገኘው?” እያለ ሲጨነቅና፤ ሲጠበብ፤ አንድ ቀን እንዳገሩ ልማድ የመንደሩን ከብት ሁሉ ከጅብና ከዘራፊዎች ሲጠብቅ እንዲያድር*

*ተራ ይደርሰዋል። ሰሞኑን ጸጥ ብሎ የከረመው ነጌሶ በዚያን ምሽት በከብት ዘራፊ ወራሪዎች ይከበባል። ያቶ ወልደየስ ልጅ ዛሬ ጀብዱ ካልሠራ መቼም ስሙ አይታደስምና እነዚያን ወራሪዎች ተኩስ ይገጥማና ሁለት ገድሎ፤ መሣርያቸውንም ማርኮ፤ እሱም ከፉኛ ቆስሎ ረዴው ይድርሳል። ድፍን ቀውት ጉድ ይልና፤ ቁስለኛን በቃሬዛ ተሸክሞ "፡ላሌ ጉማ! ጀግናው ገድሏል ዛሬ!እየተባለ፤ እየተፎከረለት ወደቤቱ ሲጓዝ፤ ሲያብሰለስለው የኖረውን*

*ብሶቱን እዚያይዝው በቃሬዛው ላይ እንዳለ "!ስሙኝ ጎበዝ! ያቶ ወልደየስ ልጅ ትንሹ ፈሪ ነው ! ፈሪ ነው! ስትሉኝ ይኸው ዛሬ ተመታሁላችሁ" አለ ይባላል።*

ለዚች ታርክ ምክንያቴ ምንድነው?በመጀምሪያ ደረጃ "ብርሃኑ ነጋ አማራን ለማዳከምና ለማጥፋት ቆርጦ የተነሣ ዘረኛ ነው። " የሚለውን ምሠረተ ቢስ ክስ የስናፍጭ ቅንጣትን የምታስቀጥ ቦታ አልሰጠውም። ከወያኔ ጋር አብሮ የፈተፈተ፤ ለኤርትራ ያደገደገ፤ አቋሙ ያልተጣራ " ለሚለው ክስ መልሱን ለመጠት ዶከተር ብርሃኑ ይጨነቅበት። ሌላው ሲታማበትና ሲወቀስበት የቆየው " ወሬ ያብዛል፤ በሥራው ላይ ግን የለበትም፤ ወንድ ከሆነ በርግጥ በትጥቅ ትግል የሚያምን ከሆነ፤ እዚህ ቁጭ ብሎ ከሚያወራ ለምን አገር ገብቶ አይዋጋም?ማውራት ሌላ፤ ያወሩትን በሥራ ላይ ማዋል ደግሞ ሌላ ነገር ነው" እየተባለ ብዙ ተብጠልጥሏል። ከእንግዲህስ አሁን ምን ብለን እናውራ? ዛሬ ብርሃኑ ነጋ ከፍተኛ አመራሮቹን አስከትሎ ኤርትራ በረሃ ገብቷል። በመግባቱ የላሸቀው የሕዝብ ወኔ አንሰራርቷል። ወንዶምቻችንና እህቶቻችን ሕይወታቸውን አሳልፈው ለስመጠት አሰፍስፈዋል። ወደኋላ ሊመልሱ በማይደርሱበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። አንድ ጊዜ የጠመንጃን ምላጭ ጎትቶ የተተኮሰችን ጥይት ነይ ተመለሽ አይሏትም። ታመነም አልታመነ አሁን ከወያኔ ጋር ደም እተቃባን ነው። ከናት አገር ፍቅርና ለምንወደው ወገናችን መብቱን ለማስጠበቅና፤ ክብርና ሞግሱን እንዲጎናጸፍ ለማድረግ፤ ለዶክተር ብርሃኑ ነጋ ያለን ጥላቻ ሊያግደን ይችላልን? እኔ እንኳን ብርሃኑ ነጋን የሚያል ጥሩ ኢትዮጵያዊ፤ በቆመበት የሚያኮራ ወገን ይቅርና፤ መንግሥቱ ኃይለማርያም ጦር አስከትሎ ወያኔን ሊወጋ ወደ አዲስ አበባ ቢገስግስ አብሬው ተስልፌ ወያኔ አይቀጡ ቅጣት እቀጣዋለሁ። ለወያኔ ያለኝ ጣላቻ ለደርግና ለመንግሥቱ ኃለማርያም ያለኝንን ቂም ያስረሳኛል። (ከወያኔ መመታት በኋላ መንግሥቱን ምን ታደርገዋለህ ብላችሁ እንዳጠይቁኝ) ዶክተር ብርሃኑ ወሬ በቃ ብሎ "ጎራው ቤቴ" ብሏል።

ከጎኑ ቆመን አይዞህ በርታ እያልን ሙሉ ድጋፋችንን ልንሰጠው ይገባናል። ከእንግዲህ ጉዞው ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ አይደለም። ማን ያውቃል ይሚቀጥለው የኢሳት ሰበር ዜና "የአርበኞችግንቦት ሰባት ኃይሎች ጠቅላላ ጎንደርን ተቆጣጠሩ፤ አምስት ከፍተኛ የወያኔ የጦር አዛዦች ተማረኩ፤ የወያኔ ሠራዊት የጠመንጃውን አፈሙዝ ወደ አለቆቹ አዞረ፤ጎጃምም ክተት ብሏል፤አዲስ አበባ በፍርሃት እየንቀተቀጠች ነው።" የሚል ይሆናል። " ሠልፍ የጀግና ነው፤ ድል የእግዚአብሄር ነው።" ድሉን የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅርብ ይጎናጸፉል።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!

**ይፍሩ ኃይሉ**
yhailu05@yahoo.com